DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# አድልዎ ያለማድረግ ማስጠንቀቂያ

በ1964 የሲቪል መብቶች ሕግ ርዕስ VI፣ በ1972 የትምህርት ማሻሻያዎች ርዕስ IX፣ በ1973 የሪሃቢሊቴሽን ሕግ ክፍል 504፣ በ1975 በዕድሜ ላይ የተመሰረተ አድልዎ ህግ፣ በ1990 የአሜሪካዊያን አካል ጉዳተኞች ሕግ ርዕስ II፣ በ2008 በጀነቲክ/በዘር መረጃ አድልዎ ያለማድረግ ሕግ እና በ1977 የዲሲ የሠብዓዊ መብቶች ሕግ እንዲሁም በነዚህ ህጎች ላይ በቀጣይ በተደረጉት በሁሉም ማሻሻያዎች መሠረት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች በትምህርት መርሐግብሮቹ ወይም (በትምህርት ቤቱ የሚፈጸመውን የስራ ቅጥር ወይም የትምህርት ምዝገባን ጨምሮ) በሚያከናውናቸው ተግባራት ውስጥ በትክክል በሚታይ ወይም ነው ተብሎ በታሰበ ዘር፣ ቀለም፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ኃማኖት፣ ብሔራዊ ማንነት፣ ጾታ፣ እድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በግላዊ አቋም፣ በወሲባዊ ዝንባሌ፣ በሥርዓተ ጾታ ማንነት ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ በቤተሰባዊ ኃላፊነቶች፣ በፖለቲካ ውግንና፣ በጀነቲክ መረጃ፣ በገቢ ምንጭ፣ በብድር መረጃ ወይም ሁኔታ የቤት ውስጥ ድብደባ ተጠቂ ወይም የቤት ውስጥ ድብደባ ተጠቂ የቤተሰብ አባል፣ በወሲባዊ ጥፋት ወይም የጥፋት ተሳትፎን መሰረት በማድረግ አድልዎ አይፈጽምም። ወሲባዊ ትንኮሳ በ1972 የትምህርት ማሻሻያዎች ርዕስ IX መሰረት የተከለከለ ጾታ ላይ የተመሰረተ የአድልዎ ዓይነት ነው። በተጨማሪም ከላይ በተዘረዘሩት ጥበቃ በሚደረግላቸው በማናቸውም ላይ በመመስረት የሚፈጸም ትንኮሳ የተከለከለ ነው።

የተጠቀሱትን ህጎች በመጣስ የሚፈጸም አድልዎ ተቀባይነት አይኖረውም። ህግ በሚጥሱ ጥፋተኞች ላይ የስነስርዓት እርምጃ ይወሰዳል። የDCPSን አድልዎ ያለመፈጸም ፖሊሲዎች በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና/ወይም አቤቱታዎች ከዚህ በታች የቀረበውን መመርያ በመጠቀም ይታያሉ።

**የ1972 የትምህርት ማሻሻያዎች ርዕስ IX እና የማስፈጸሚያ ደንቦቹ DCPS ተማሪዎቹንና ሌሎችን ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ ጾታ ላይ ከተመሰረተ አድልዎ ለመከላከል ዓይነተኛ እና ቀጣይነት ያላቸውን እርምጃዎች እንዲወስድ ይፈልጋል። ሊኖር የሚችልን በጾታ ላይ የተመሰረተ ትንኮሳ በተመለከተ ጥያቄዎች እና/ወይም ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የትምህርት ቤት ኀብኘዎች/እንግዶች እና የአጠቃላይ ህዝቡ አባላት ከሚከተሉት ጋር ግንኙነት ማድረግ አለባቸው፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ርዕስ IX አስተባባሪ<br>አጠቃላይ የአማራጭ ውሳኔ እና እኩልነት (CARE) ቡድን<br>የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools)<br>1200 First St NE, 9th Floor<br>Washington, DC 20002<br>ስልክ፡ (202) 442-5404<br>ኢሜይል፡ dcps.care@k12.dc.gov | *ወይም* | *የሲቪል መብቶች ረዳት ጸሀፊ*<br>*የዩኤስ የትምህርት መምሪያ* (U.S. Department of Education)<br>400 Maryland Ave, SW<br>Washington, DC 20202-1100<br>ስልክ፡ 1-800-421-3481 ኢሜይል፡ OCR@ed.gov | *ወይም* | ዲሲ የሠብዓዊ መብቶች ጽ/ቤት (DC Office of Human Rights)<br>441 4th St NW, Suite 570N<br>Washington, D.C. 20001<br>ስልክ፡ (202) 727-4559<br>(ቲዲዲ፡ 1-877-521-2172)<br>ኢሜይል፡ OHR@dc.gov |

**ጾታ ላይ በመመስረት ከሚፈጸመው አድልዎ ውጪ፣ ሊፈጸሙ ከሚችል የ DCPS የጸረ-አድለዎ ፖሊሲዎች ጥሰት ጋር በተያያዘ ጥያቄዎች እና/ወይም ቅሬታ ያላቸው ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የትምህር ቤት ኀብኘዎች/እንግዶች እና የአጠቃላይ ማህበረሰቡ አባላት ከሚከተሉት ጋር ግንኙነት ማድረግ አለባቸው፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አጠቃላይ የአማራጭ ውሳኔ እና እኩልነት (CARE) ቡድን<br>የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools)<br>1200 First St NE, 9th Floor<br>Washington, DC 20002<br>ስልክ፡ (202) 442-5405<br>ኢሜይል፡ dcps.care@k12.dc.gov | *ወይም* | *የሲቪል መብቶች ረዳት ጸሀፊ*<br>*የዩኤስ የትምህርት መምሪያ* (U.S. Department of Education)<br>400 Maryland Ave, SW<br>Washington, DC 20202-1100<br>ስልክ፡ 1-800-421-3481<br>(ቲዲዲ፡ 1-877-521-2172)<br>ኢሜይል፡ OCR@ed.gov | *ወይም* | ዲሲ የሠብዓዊ መብቶች ጽ/ቤት (DC Office of Human Rights)<br>441 4th St NW, Suite 570N<br>Washington, DC 20001<br>ስልክ፡ (202) 727-4559<br>(ቲዲዲ፡ 1-877-521-2172)<br>ኢሜይል፡ OHR@dc.gov |

**ከስራ ቅጥር ወይም ከሰራተኞች ጋር በተያያዘ ሊፈጸም የሚችልን የDCPS የጸረ-አድልዎ ፖሊሲዎችን ጥሰት በተመለከተ ጥያቄዎች እና/ወይም ቅሬታ ያላቸው የ DCPS ሠራተኞች ከሚከተለው ጋር መገናኘት አለባቸው፡**

| | | |
|---|---|---|
| *እኩል የሥራ ቅጥር ዕድል ቡድን*<br>*የሠራተኞች አስተዳደር እና የሠራተኛ ግንኙነቶች ጸ/ቤት* (LMER)<br>የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች (District of Columbia Public Schools)<br>1200 First St NE, 10th Floor<br>Washington, DC 20002<br>ስልክ፡ (202) 442-5424<br>ኢሜይል፡ dcps.eeo-ada@k12.dc.gov | *ወይም* | የዩኤስ እኩል የሥራ ቅጥር እድል ኮሚሽን (U.S. Equal Employment Opportunity Commission - EEOC)<br>131 M St NE, 4th Floor, Suite 4NWO2F<br>Washington, DC 20507<br>ስልክ፡ 1-800-669-4000<br>ኢሜይል፡ info@eeoc.gov<br>ድረ-ገጽ፡ www.eeoc.gov |

**በተፈጸመ አድልዎ ላይ ሪፖርት ባቀረቡ ወይም ተፈጽሟል በተባለ አድልዎ ላይ ማናቸውንም ምርመራ ባደረጉ ሰዎች ላይ የሚፈጸምን የብቀላ ርምጃ DCPS አይታገስም። ሊፈጸሙ በሚችሉ የሕግ፣ የደንብ ወይም የፖሊሲ ጥሰቶች ላይ በቅን ልቦና እና ጉዳት ከማድረስ ሀሳብ ውጪ በሆነ ፍላጎት ሪፖርት የሚያደርጉ ግለሰቦች ላይ የማስፈራራት፣ የዛቻ፣ የማስገደድ፣ የአድልዎ ድርጊት ሊፈጸምባቸው ወይም የብቀላ እርምጃ ሊወሰድባቸው አይገባም። የብቀላ እርምጃ ተወስዶ ከተገኘ፣ ሰዎች ከስራ መሰናበትን ጨምሮ እስከዚህ የሚደርስ ተገቢ የሥነ ስርዓት ርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል።**

*ተማሪዎች ወይም ተማሪዎች/ሠራተኞች የተሳተፉበት ማናቸውንም የ DCPS ጸረ-አድልዎ ፖሊሲዎችን በመጣስ ሊፈጸም የሚችል አድልዎ መኖሩን የሚያውቅ ወይም አሳማኝ በሆነ መልኩ ሊያውቅ የሚገባው የ DCPS ሠራተኛ እንደ አስፈላጊነቱ ከርዕስ IX አስተባባሪ እና/ወይም ከአጠቃላይ አማራጭ ውሳኔ እና እኩልነት (CARE) ቡድን ጋር መገናኘት አለበት። ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ የ DCPS ሠራተኛ ብቻ የተሳተፈበት በጾታ ላይ የተመሰረተ ሊፈጸም የሚችል አድልዎ መኖሩን የሚያውቅ ወይም አሳማኝ በሆነ መልኩ ማወቅ ያለበት የ DCPS ሠራተኛ ከ LMER ጋር በተለይም ከሚከተለው ጋር ግንኙነት ማድረግ አለበት፡ የወሲባዊ ትንኮሳ ኃላፊ